# እሽ አትበሉኝ የሹም ዶሮ ነኝ ?!

**ከተሾመ ነገራ(**negerateshome@yahoo.com)

ሰሞኑን የአሜሪካ ድምፅ ሬድዮ የአማርኛ ፕሮግራም እና የጀርመን ድምፅ ሬድዮ የአማርኛው አገልግሎት ባሰራጩት ዜናና ቃለምልልስ አዲስ ነገር የሚባለው ሳምንታዊ የግል ጋዜጣ ህትመቱን ማቋረጡንና የጋዜጣው ዋና አዘጋጅን ጨምሮ የተወሰኑ ኤዲተሮች ሀገር ጥለው መውጣታቸውን አስደምጠውናል ፡፡ ዘገባውን የሃገር ውስጥና የውጭ መገናኛ ብዙሃን ተቀባብለው አስተጋብተውታል፡፡ አንዳንዶቹ የግል ጋዜጦች ሪፖርታዥ መሰል ሰፊ ሃተታዎችን በማውጣት "ለስደተኞቹ"ጋዜጠኞች ከንፈር መጠዋል፡፡ አንዳንዶቹ የእለቱለት ነጠላ አዘቅዝቀው ፎጣ ታጥቀው ቱቢት አስረውና ፅናቱን ተመኝተው ወደመደበኛ ስራቸው ተመልሰዋል ፡፡ በጣም ጥቂት ዘመድ አዝመድ ነን ባዮች ግን ደረት ደስቀዋል፤ ማስለቀስ ቢሳናቸውም እንኳ ለራሳቸው ሀቅ ስቅ ብለው አልቅሰዋል ፡፡ ብዙዋቹ ግና በጋዜጠኞቹን ኩብለላ ዙርያ የተምታታና ያልጠራ ብዥታ መኖሩን በሚያመላክት መንገድ ብያኔያቸውን በይደር ማቆየት መርጠዋል ፡፡ አንዳንድ ለሚድያ ተቆርቋሪ ነን ባይ ተቋማትና ዲፕሎማቶች ግን ( አለም አቀፍ የፕሬስ ተቋም (IPI) እና የድንበር የለሽ ዘጋቢዎች ተቋምን (RSF) መሰል የውጭ ሃገር ድርጅቶችና እና የአሜሪካ ኤምባሲ) **እንደወትሮው** ወዲያ ወዲህ ዞረው ጉዳዩን ለማጣራት አንዳችም ጥረት ሳያደርጉ የኮብላይ ጋዜጠኞቹን ስሞታ ያስደመጠው ፕሮግራም እንዳበቃ በብርሃን ፍጥነት የተዘጋጀ የጥድፊያ መግለጫዎችን አውጥተዋል፡፡

በ1997 አ ም በነፃ ጋዜጦች ላይ የተካሄደው "የአፈና እርምጃ " በቀጣዩ ምርጫም አገርሽቶበታል በማለት መግለጫ ያወጣው RSF የተባለው ተቋም ሲሆን ይኸው ድርጅት ሃገሪቱ ለቀጣዩ ምርጫ ዝግጅት በምታደርግበት በአሁኑ ወቅት በነፃው ፕሬስ እንቅስቃሴ ላይ "አሸማቃቂ የፍርሃት ድባብ" መፈጠሩ ተገቢ አይደለም በማለት

ከIPI ጋር ተመሳሳይ የሆነ ኮናኝ መግለጫ አውጥቷል ፡፡ የዚሁ ተቋም ሃላፊም የጋዜጠኞቹ ከሃገር መውጣት የቀጣዩን ምርጫ ነፃነት፣ ሚዛናዊነትና ዴሞክራሲያዊነት ጥያቄ ውስጥ ከቶታል በማለት የገለፀ ሲሆን IPI የተባለው ድርጅትም በተመሳሳይ የአዲስ ነገር ጋዜጣ የስራ ባልደረቦች ከአገር መውጣት በመጪው ምርጫ ወቅት መንግስት የሚተቹትን ጋዜጠኞች ዝም ለማሰኘት ያለውን ፍላጎት ያሳያል የሚል መግለጫ አውጥቷል ፡፡ ጋዜጠኞቹ ላደረባቸው ፍርሃትና ስጋት መንግስት መተማመኛ ከሰጠ ስራቸውን ለመጀመር እንደሚችሉ የድርጅቶች መግለጫ

ይጠቁም እንጂ ባለፈው ማክሰኞ ለንባብ ለበቃው ለአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ የአዲስ ነገር ባለቤት የነበረው አሳታሚ አብይ ተክለ ማርያም ግን ብርቱካን ሚደቅሳ የምትፈታ ከሆነ ፣ ሌላ ነፃ የምርጫ አስፈፃሚ ተቋም ከተቋቋመ እና ገዳቢ ናቸው የሚላቸው ሶስቱ ህጎች የሚሻሩ ከሆነ ብቻ ጓደኞቹ ወዳገር ሊመለሱ ጋዜጣዋም ስራ ልትጀምር እንደምትችል አስታውቋል፡፡ ከነዚህ መግለጫዎች ብዙም ያልተለየው የአሜሪካ ኤምባሲ መግለጫም ወከባና ማስፈራሪያ አገር አስለቅቆናል የሚለው የጋዜጠኞቹ እሮሮ አሳስቦኛል የሚል ይዘት ነው ያለው ፡፡

የጋዜጣዋ አዘጋጆች "ጋዜጣው መታተም ከጀመረ ግዜ ጀምሮ ከመንግስት የሚደርስብንን ጫናና ወከባ መቋቋም አልቻልንም ፣ ካለፉት አራትና አምስት ወራት ወዲህ ጋዜጠኞቻችንን ለሽማቀቅና በርካታ ማስፈራሪያና ማስጠንቀቂያ አዘል ፅሑፎች በመንግስታዊው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ወጥተዋል፤ በመንግስት ቴሌቪዥን አማካይነትም በጋዜጣችን ላይ ያነጣጠረ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ሊከፈትብን መሆኑን መረጃ ደርሶናል፤ የሃገሪቱ የደህንነት ተቋም በመረጃ ምንጮቻችንና ጋዜጠኞቻችን ላይ ስልኮችን በመጥለፍም ጭምር ክትትል ያደርጋል ፣ ከአንድ ከፍተኛ የደህንነት ባለስልጣንም የስልክ ማስጠንቀቅያ ተሰጥቶናል፣ በአዲሱ የፀረ ሽብርተኛነት ህግ ከባድ የወንጀል ክስ ሊመሰረትብን ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን በታማኝ ምንጮቻችን ተነግሮናል ፡፡ ስለሆነም በነፃነት መስራት የማንችልበትና ደህንነታችንም አደጋ ላይ ሊወድቅ የሚችልበት ሁኔታ እየተቃረበ መምጣቱን ስላረጋገጥን ከሀገር

ለመውጣት ተገድደናል " ማለታቸውን ሶስት ተከታታይ ፕሮግራሞች ከፈጀው የቪኦኤ መርዶ መረዳት ችያለሁ ::

የኮሚኒዩኬሽን ጉዳዮች ፅህፈት ቤት ሚኒስትር አቶ በረከት ስምኦን መንግስት በጋዜጣው ላይ ምንም ዓይነት ጫናና ግፊት አድርጎ እንደማያውቅ ፤ የአዲስ ነገር አዘጋጆችንም በማናቸውም ጥፋት ለመክሰስ ዕቅድ እንዳልነበረውና ጋዜጣው መቼም ቢሆን የመንግስት ዒላማ እንዳልነበረ በመግለፅ በማስረጃ ያልተደገፈውን የአዘጋጆቹን ስሞታ አጣጥለውታል :: መንግስት ምርጫ እየተቃረበ በመጣበት በአሁኑ ወቅት ከግል ሚዲያዎች ጋር ምንም ዓይነት ግጭት የመፍጠር ዕቅድ እንደሌለው ያረጋገጡት አቶ በረከት መንግስት በጋዜጠኞቹ ላይ ሊያቀርብ ያሰበው አንድም የወንጀል ክስ አለመኖሩን አስታውቀዋል ::

እስቲ ያዲስ ነገር ጋዜጣ አዘጋጆችን እሮሮና የመንግስትን ምላሽ በንፅፅር በማየት ስሞታቸው ውሃ ያነሳ እንደሆነ ለማየት እንሞክር ::

የጋዜጣዋ አንባቢ እንደመሆኔ በበኩሌ የአዲስ ነገር ጋዜጣ አዘጋጆች ከአገር ከመውጣታቸው አስቀድሞ መንግስት ጫና አድርሶብናል አዋክቦናል፡ ይሰልለናል ወዘተ የሚል ስሞታ ያቀረቡበትን አንድም ዘገባ ወይም መጣጥፍ አንብቤ አላውቅም ::

እስከማውቀው ድረስ መንግስት ለሃገሪቱ ሚድያዎች ምቹ የስራ ደባብ ለመፍጠር ተከታታይ ጠቃሚ እርምጃዎችን ወስዷል:: ከመንግስታዊ የስራ ክንዋኔዎች ውሳኔዎችና እርምጃዎች በስተጀርባ ያሉ ምክንያቶችን ለማብራራትና ወቅታዊ መረጃዎችን ለህዝብ ለማስተላለፍ መንግስት ባዘጋጃቸው ሳምንታዊ የፕሬስ ጥቆማና ማብራሪያ መድረኮች የአዲስ ነገር ጋዜጣም ከሌሎች ሚዲያዎች ጋር ሲሳተፍ መከረሙን በሚገባ አውቃለሁ :: ከዚህ በተጨማሪም ጋዜጣው የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር በየሁለት ወሩ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ለጋዜጠኞች ማብራሪያ በሚሰጡበት ቋሚ መድረክ ላይም የመሳተፍ እድል እንዲያገኝ መደረጉ ይታወሳል :: የጋዜጣው ሪፖርተሮች በጠየቋቸው ጉዳዮች ላይ ከመንግስት መስሪያቤቶችና ከፍተኛ ሃላፊዎች መረጃ የሚያገኙበት መብትና እድልም ነበራቸው :: አልተጠቀሙበትም ወይም ለመጠቀም አልመረጡም እንጂ ::

እንደኔ እንደኔ እነዚህና ሌሎች ለስራቸው አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች ተመቻችተውላቸው እያለ "መንግስት በስራችን ላይ ጫና ፈጥሮብን ቆይቷል" በማለት የጋዜጣዋ አዘጋጆች የሚያቀርቡት የሃሰት ውንጀላ ከመኮብለላቸው በስተጀርባ ሊገልፁት የማይሹት ሌላ ምክንያት መኖሩን በግልፅ አመላካች ነው ::

ባለፈው አመት በሀገሪቱ ውስጥ በሚሰሩ ቋሚ የውጭ ሚድያ ወኪሎች ማህበር በተዘጋጀ የመልካም ጋዜጠኝነት ሽልማት አሸናፊ ለመሆን የበቃው ፅሁፍ በአዲስ ነገር ጋዜጣ ላይ ታትሞ የወጣ ፅሁፍ እንደነበረ ራሳቸው አዲሰ ነገሮች በኩራት መዘገባቸው ይታወሳል :: ታድያ የእጩ አሸናፊ ፅሁፎችና ፎቶዎች መራጭ ቦርድ ውስጥ ሳይቀር በተወካዮች አማካይነት የተሳተፈና በህዝብ መገናኛ ብዙሃን ሽፋን ባገኘው ስነ ስርአት ላይም ሽልማቱን በሰጡ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን አማካይነት ተሳትፎ ያደረገን መንግስት ዛሬ ተመልሶ ያጥላላናል፣ ያሳድደናል ፣ ወከባ ይፈፅምብናል ብሎ መወንጀል እራሳቸውን አዲስ ነገሮችን ባጉራሽ እጅ ነካሽነት ለትዝብት ይዳርጋቸዋል ::

ከሁሉም በላይ ለትዝብት የሚዳርገው ግን በአሁኑ ወቅት ከአገር የወጡት ሁለቱ የጋዜጣው ዋናና ምክትል አዘጋጆች ከጥቂት ሳምንታት በፊት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በቀረበ ፕሮግራም ላይ “ ምንም አይነት የሳንሱር አሰራር አጋጥሞን አያውቅም ፣ በስራችን ላይ ማንኛውም የመንግስት አካል ጣልቃ ገብቶብን አያውቅም እስካሁን ይህን አትሙ ያንን አታትሙ ያለን አንድም የመንግስት አካል የለም :: ኢትዮጵያ ውስጥ ከተደረጉት ለውጦች ዋነኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች የመደራጀት ነፃነት የፕሬስ ነፃነት ናቸው” በማለት በአፅንኦት እንዳልተናገሩ ዛሬ ሳንሱር ዛቻና ወከባ አላሰራ ብሎን ከአገር ለመውጣት ተገደናል በማለት ያለአንዳች ሃፍረት ባደባባይ ተጣራሽ ንግግር ማሰማታቸው ነው ::

ሌላው አስተዛዘዛቢ ነገር እኒህ ክፉ የዝንጋታ ደዌ የተጠናወታቸው የጋዜጣዋ አዘጋጆች ከሃገር የመውጣታችን ምክንያቶች ናቸው በማለት ሶስት ቀናት ሙሉ ሲያኸ ዥጎደጉዷቸው የነበሩ ቅሬታዎችን ረስተው ከተሰተካከሉን እንመለሳለን የሚሏቸውን ሌሎች የኩብለላ ምክንያቶች በቀናት ልዩነት ይዘው ብቅ ማለታቸው ነበረ ፡፡ አዘጋጆቹ ወደ ሃገር በመመለሰ ስራቸውን ለመጀመር የደረደሩዋቸው ቅድመ ሁኔታዎች ከሃገር ለመውጣታችን ምክንያቶች ናቸው ካሏቸው" እክሎች " መቅረት (" የወንጀል ክስ ዝግጅት እና አስተዳደራዊ ወከባ ") ጋር ጨርሶ ግንኙነት የሌላቸው መሆናቸውን ለመታዘብም ችለናል፡፡ ብርቱካን ሚደቅሳ ካልተፈታች ፣ ምርጫ ቦርድ ፈርሶ እንደ አዲስ ካለተቋቋመ እና የበጎ አድራጎት፣ የሚድያና የፀረ ሽብርተኝነት ህግጋት ካልተሻሩ አንመለስም የሚሉ ቅድመ ሁኔታዎቻቸው ደግሞ ከፈጠራ የኩብለላ ምክንያቶቻቸው ጋር ጨርሶ የማይያያዝ ሌላ ፖለቲካዊ ግብን ለማራመድ አስበው የወጡ መሆነአቸውን በግልፅ አመላካች ነው ፡፡ እጅግ የሚያደንቃቸውን ዶ/ረ ብርሃኑ ነጋን በነቢበም በምግባርም ለመከተል የቆረጠ መሆኑን አገሬን ከጥፋት ለማዳን ስል ሰላማዊ ትግል አያዋጣም ካሉ ንቅናቄዎች ጋርም እሳተፋለሁ በማለት አሳታሚ አብይ ተ/ማሪያም ለአውራምባ ታይምስ መግለፁ ይህንኑ ጥርጣሬ የሚያጠናክር ሌላ ማስረጃ ነው ፡፡

ሌላው የጋዜጣዋ አዘጋጆች አስገራሚ ስሞታ ደግሞ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የማጥላላትና የማስፈራራት ዘመቻ ተከፈቶብናል በማለት የሚያቀርቡት ወቀሳ ነው ፡፡
ይህን በተመለከተ እነ መጋቢ መስፍን ነጋሽ ጥቃት አደረሱብን የሚሉዋቸውን ፅሁፎች ይዘትና ግድፈቶቻቸውን በቅርበት ከማየት ይልቅ ፀሃፊው ወይም ከፅሁፎቹ በስተጀርባ ያለው ግለሰብ ወይም አካል ማን ይሆን በሚሉ መላምቶቻቸው ላይ እንድናተኩር ነው የሚፈልጉት ፡፡ ውሎ አድሮ ሰዎቹን ካገር ያስፈረጠጡ ፅሁፎች ምን ይሆን የሚሉት እያለ ሰዉ የተከሳሾቹን ፅሀፎች ይዘት ማየቱ ስለማየቀር እንዲህ አይነቱ የክርክር ሽፍጥ እነ መጋቤ መስፍንን ብዙ ርቀት እንደማያራምዳቸው ገልፅ ነው ፡፡

ጋዜጣቸውን አስመልክቶ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የቀረቡት ሂሶች በጋዜጣው ርእሰ አንቀፅ ላይ የሰፈሩ ሳይሆኑ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የዜጎችን አስተያየቶች ለማስተናገድ ጋዜጣው ባዘጋጀው አምድ ስር የወጡ ፅሁፎች እነደነበሩ ይታወሳል፡፡ ፅሁፎቹ ከሙያ ስነ ምግባር መስፈርቶች አንፃር ጋዜጣው ያታይበታል በተባሉ ግድፈቶች ላይ ያተኩሩና የግድፈቶቹን መንስኤዎችና ጎጂ ውጤቶች በትንታኔ የሚያብራሩ በግለሰቦች የተፃፉ አስተያየቶች ነበሩ ፡፡ ለአብነትም የጋዜጣዋ አዘጋጆች ዘመቻ ተከፍቶብናል ብለው የሚያማርሩበት አንዱ ፅሁፍ በአንድ ወቅት ጊዜው ያለፈበትና የቀረ ነው ያሉትን የሚዛናዊነት እሴት ጋዜጣችን አትከተልም በማለት "አዲስ ነገር ሚዛናዊ አይደለችም" በሚል ርእሰ የፃፉትን ርእሰ አንቀፅ ከሙያው አንፃር የሚተች አስተያየት ነበር ፡፡ በማንኛውም ዴሞክራሲያዊ ስርአት መገናኛ ብዙሃን ከህዝብ ሂስ እና ትችት የተጋረዱ አይነኬ ተቋማት አለመሆናቸው ይታወቃል ፡፡ ተገቢ የሆነው ሙያዊና ዴሞክራሲያዊ አሰራር ተመሳሳይ ትችት የቀረበበት አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ እንዳደረገው ትችቱን ባወጣው ጋዜጣ ወይም በራሳቸው ህትመት ላይ ምላሽ መስጠት እንጂ ምናባዊ የሴራ ንድፈ ሃሳብን በማዳወር ከክርክር መሸሽ አልነበረም ፡፡ታድያ ስራዬ በገኘው ፓርቲና በሌሎች ተቋማት ላይ የሰላ ሂስ መሰንዘር ነው እያለ የሚኩራራ ጋዜጣ ሂስ በደጃፌ ዝር እንዳይል “ እሽ አትበሉኝ የሹም ዶሮ ነኝ” ማለቱ አንድም ዝቅተኛ የሙያ ግንዛቤውን አሊያም በዴሞክራሲያዊው የመቻቻል እሴት አለመታነፁን intolerance ከማሳየት ያለፈ ሌላ ትርጉም አይኖረውም ፡፡

እንዲያው ለክርክር ሲባል ግን መንግስት ነው የሚፅፍብን የሚለው የአዲስ ነገሮች ስሞታ ልክ ነው ብለን ብንነሳ ከቆመጥ ክርክር ይልቅ የሃሳብ ፍልሚያን መርጦ በፅሁፍ የሚከራከር መንግስት ወይም ባለስልጣን መኖሩ ከማስደስት ይልቅ ለምን እንደሚያስከፋ አዲሰ ነገሮች ግልፅ ቢያደርጉልኝ በወደድኩ ፡፡

በሃገራችን ተቃውሞን ለማስቀረት ሲባል የደህንነት ተቋማት ዜጎችን በመሰለል በማስፈራራትና በማሸማቀቅ ተግባር ላይ የሚሰማሩበት አሰራር ከአምባገነናዊው ወታደራዊ አገዛዝ ጋር መቃብር ከወረደ ሁለት አስርት አመታትን መቆጠራቸውን ምናልባት አዲስ ነገሮች እንጂ ነፃነቱን ሲያጣጥም የሚውለው እያንዳንዱ ዜጋ ግን በሚገባ ያውቀዋል፡፡ የመናገርና ሃሳብን በነፃ የመግለፅ ነፃነት በሃገራችን የተሟላ ህገ መንግስታዊና ተቋማዊ ዋስትና ማግኘቱ የማይታበል ግዙፍ ሃቅ ነው ፡፡ ዛሬ

በአይነትና በይዘት በርካታ የሆኑ የፕሬስ ውጤቶች ለስርጭት መብቃታቸው የፕሬስ ነፃነት በማይቀለበስ ደረጃ ተግባራዊና ተቋማዊ መሰረት ያገኘ ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው ፡፡
ህገ መንግስቱ ማንኛውንም አይነት ቅድመ ምርመራ ያስወገደ ከመሆኑም በላይ ለዜናና መረጃ ማሰባሰቡ ሂደት news gathering process የተሟላ ህጋዊ ጥበቃ ለመስጠት የመረጃ ምንጮች ምስጢራዊነት እንዲጠበቅና ጋዜጠኞች የመረጃ ምንጮቻቸውን ማንነት ለመግለፅ እንዳይገደዱ አስፈላጊውን ጥበቃ የሚሰጥ የህግ ዋስትናም በሃገራችን ተበጅቷል ፡፡ ነፍሷን ይማረውና አዲስ ነገር ራሷ የዚህ ነፃነት ትግበራ ማሳያ የሆነች ጋዜጣ ነበረች ፡፡

ሃቁ ይህ ሆኖ ሳለ ለነዚህ ህገ መንግስታዊ ትእዛዞች መከበር የቆሙ መንግስታዊ ተቋማት በዜና ዝግጅት ስራችን ውስጥ ጣልቃ በመግባት ያስፈራሩናል በጋዜጠኞችና በምንጮቻችን ላይም ከትትል ያደርጋሉ በማለት የጋዜጣው አዘጋጆች የሚሰነዝሩት ወቀሳ አንዳችም የእውነት መሰረት እንደሌለው አዘጋጆቹ ራሳቸው እስከዛሬ በስራቸው ውስጥ ምንም አይነት መንግስታዊ ጣልቃ ገብነት የማይደረግ መሆኑን በማረጋገጥ ከሳምንታት በፊት በይፋ ከሰጡት ምስክርነት የበለጠ አስረጅ አይገኝም ፡፡

የአዲስ ነገር ጋዜጣ አዘጋጆች መንግስት በአዲሱ የፀረ ሽብርተኝነት ህግ ክስ ሊመሰርትብን ዝግጅት እያደረገ ስለሆነ ሃገር ለቀን ተሰደናል በማለት የሚያቀርቡትን ስሞታ እስቲ በቅርበት ለማየት እንሞክር ፡፡ ማንም እንደሚያውቀው እስካሁን ድረስ ላይ በአዲሱ የፀረ ሽብርተኛነት ህግ ላይ የተመሰረተ ክስ በማንም ሰው አልቀረበም፡፡ ህጉ ከህገ መንግስቱና ከአለም አቀፍ መሰረታዊ የሰብአዊ መብቶች ህግጋት ጋር እንዲጣጣም ተደርጎና የዳበረ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ባላቸው አገሮቸ ልምድ ላይ ተመስርቶ በጥንቃቄ የተቀረፀ በመሆኑ ምናልባት የታዳኝነት ደዌ ሰለባ ከሆነ ሰው በስተቀር በፕሬስ ነፃነትም ሆነ በሌሎች የዜጎች መሰረታዊ መብቶች አፈፃፀም ላይ የሚያስከተለው አንዳችም አሉታዊ ተፅእኖ ወይም ስጋት አይኖርም፡፡ በማናቸውም የአዲስ ነገር ጋዜጣ አዘጋጅ ወይም ሪፖርተር ላይ ከሽብርተኝነት ጋር የተያያዘ በፖሊስ የተከፈተ የወንጀል ምርመራ መዝገብ አለ ሲባል አልሰማንም ፡፡ ቢኖር ኖሮ እንኳንስ ዘንቦብሽ ነውና አዲስ ነገሮችም ሆኑ ወዳጆቻቸው ሳይዘገቡ ሳያወግዙ ያለፉታለ ብዬ አላስብም ፡፡ በሃገራችን የወንጀል ህግ ስርአት መሰረት በማንም ተጠርጣሪ ላይ የፖሊስ ምርመራ ሳይከናወን የማንኛውም አይነት የወንጀል ክስ ዝግጅት (የአሸባሪነት ክስንም ያካትታል) እንደማይደረግ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ከምርመራ በፊት ክስ እየተዘጋጀብን ነው የሚለው የአዲስ ነገሮች ስሞታ ከፈረሱ በፊት ጋሪው ይቀድማል ማለትን ያክል ጨርሶ ሊታመን የማይችል መሰረተ ቢስ ክስ ነው፡፡

በመጨረሻም በአበቃቀሉ ጨቅላ ደረጃ ላይ ባለው የሃገራችን የፕሬስ ኢንዱስትሪ እድገት ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ የገበያውን ውድድር መቋቋም እየተሳናቸው ከህትመት የሚንጠባጠቡ ጋዜጦችን ማየት የተለመደ ነገር ሆኖ ሳለ ለመገናኛ ብዙሃን የስራ ነፃነት ምቹ የሆነ የህግና የፖሊሲ ድባብ በመፈጠሩ ሳቢያ ከ114 በላይ የግል ጋዜጦችና መፅሄቶች በስርጭት ላይ ባሉባት ሃገር የማይሸጥ ሀሳብ ላይ ሙጭጭ በማለቱ በራሱ ከህትመት የወጣ ጋዜጣን ጉዳይ ጨርሶ እንግዳ የሆነ አዲስ ክስተት አድርጎ ማራገብ ተገቢ አይመስለኝም ፡፡